# *__ከመስጠት የሚመነጭ መስጠት__*

2 ቆሮንቶስ 8፡1 - 9፡15

***እኛ ከጠበቅነው በላይ፣ በመጀመርያ ራሳቸውን ለጌታ ሰጡ፤ ቀጥለውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን ለእኛ ሰጡ። (2 ቆሮ 8፡5 - አ.መ.ት.)***

*ስለ መስጠት መስበክና ማስተማር እጅግ በጣም ከባድ ነገር ነው! ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳችን በግልጽ ያስቀመጠውና ሐዋርያቱም በማያሻማ ሁኔታ ያስተማሩት እውነት ስለሆነ እኛም ልናስተምረው የተገባ ነው።*

__አባባል፦__ "እግዚአብሔር ሁለት እጆችን ሰጥቶናል ። አንዱን ለመቀበል ሲሆን ሁለተኛውን ደግሞ ለመስጠት ነው።" **(ቢሊ ግራሃም)**
"የምንሰጠው ያለንን ነገር በቻ ሳይሆን ራሳችንንም ጭምር ነው። " **(ጆሴፍ መርስየር)**

ጳውሎስ 2 ቆሮንቶስ 8 እና 9 ን የጻፈው በኢየሩሳሌም የሚገኙ ክርስቲያኖች ለደረሰባቸው ችግር የቆሮንቶስ ሰዎች ማሰባሰብ ጀምረው የነበረውንና ያልጨረሱትን የገንዘብ መዋጮ ጉዳይ ከዳሩ እንዲያደርሱት ለማሳሰብ ነው። ይህንን ለማድረግ በመቄዶንያ ያሉትን አብያተክርስቲያናት (የፊልጵስዩስና የተሰሎንቄ አብያተክርስቲያናት) ምሳሌነት ሲገልፅላቸው እንመለከታለን። ምንም እንኳ በመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት (ፊልጵስዩስና ተሰሎንቄ) የሚገኙት ወገኖች __ራሳቸው__ ድሆችና __በብዙ መከራ ውስጥ ያለፉ__ ቢሆኑም በችግር ውስጥ ያሉ ወገኖችን ለመርዳት __እጃቸውን በመዘርጋት በልግስና ሰጥተዋል__።

- *__መስጠት__ ሁሉም አማኞች ሊለማመዱት የሚገባ __የክርስቲያናዊ ሕይወት አንዱ አቅጣጫ ነው!__*

1. __ስለ መስጠት ልናውቃቸው የሚገቡ መሰረታዊ ነገሮች__

 1.1 __እግዚአብሔር በመጀመሪያ የሚፈልገው ያለንን ነገር (ገንዘባችንን) ሳይሆን እኛን ራሳችንን ነው።__

*"እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ __ሰውነታችሁን__ ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ህያው መስዋዕት አድርጋችሁ **ታቀርቡ ዘንድ** በእግዚአብሔር ርህራሄ እለምናችኋለሁ፤ ይህም እንደ ባለ አእምሮ የምታቀርቡት አምልኮአችሁ/አገልግሎታችሁ/ ነው።"* (ሮሜ 12፡1 - አ.መ.ት.)
*". . . **የተፈተነውን __ራስህን__** ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ።"* (2 ጢሞ 2፡15)
*"እኛ ከጠበቅነው በላይ፣ **__በመጀመርያ__** __ራሳቸውን ለጌታ ሰጡ__፤ ቀጥለውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን ለእኛ ሰጡ። (2 ቆሮ 8፡5 - አ.መ.ት. -* የመቄዶንያ ክርስቲያኖች)

ከዚህ እንደምንመለከተው እግዚአብሔር በመጀመርያ የሚፈልገው እኛን እንጂ የእኛ የሆነውን አይደለም። ምናልባት አንዱ በዘመናችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያስፈራው ነገር ሰዎች ያላቸውን ገንዘብና ሌላም ንብረት ለእግዚአብሔር ለመስጠት ፈቃደኞች ሆነው ነገር ግን ራሳቸውን ቅዱስ፣ ህያውና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ መስዋዕት አድርገው ለእርሱ ለመስጠት ፈቃደኞች አለመሆናቸው ነው። ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ከማቅረባችን የተነሳ እርሱ ሁለንተናችንን ወርሶት እያስተዳደረው ይሆን? ከዚህ የተነሳ በሕይወታችን የእርሱ ፈቃድና ሃሳብ እየተፈጸመ፣ የእርሱ መልክ እየተገለጠብን፣ በጨለማ ላሉት እንደ ብርሃን ደግሞም የሕይወት ጣዕም ላጡት እንደ ጨው ሆነን እየኖርን ይሆን?


በመምህር ማዕረጌ ሐብቱ
+251 911 47 58 42

### 1.2 ያለን ነገር በሙሉ (ንብረታችንና ገንዘባችን) የእኛ ሳይሆን የእግዚአብሔር ነው።

*"ምድርና ሞላዋ ለእግዚአብሔር ናት፥ ዓለምም በእርስዋም የሚኖሩ ሁሉ።" (መዝ 24፡1)*
*"ዓለምና ሞላው የእኔ ነውና።" (መዝ 50፡12)*
*"ምድር ሁሉ የእኔ ናትና" (ዘጸ 19፡5)*
*"ምድርና በእርስዋ የሞላባት ሁሉ የጌታ ነውና።" (1 ቆሮ 10፡26)*
*". . . ገንዘባቸውም ሁሉ በአንድነት ነበር እንጂ ካለው አንድ ነገር ስንኳ የራሱ እንደሆነ ማንም አልተናገረም።" (ሐዋ 4፡32)*

እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በሁለት አቅጣጫ ሊረዱን ይችላሉ። እነዚህም፡-
ሀ) ለእግዚአብሔር በምንሰጠው ነገር የእኛ የሆነውን ነገር እንደሰጠን የምናስብና በዚህም የምንመካ ካለን ይህንን የተሳሳተ አስተሳሰባችንን እንድናስተካክል ይረዳናል። ምድርና ሞላዋ በውስጥዋም ያለው ሁሉ በባለቤትነት ደረጃ የእግዚአብሔር ነው። እኛ ባለአደራዎች ነን። የምንሰጠው የራሱን የእግዚአብሔርን ነው።
ለ) ለእግዚአብሔር ለመስጠት እጅግ የምንሳሳና የምንስገበገብ ብንኖር ከዚህ የስስት እስራት እንድንፈታ ይረዳናል። እግዚአብሔር ጉልበት፣ ጤናና እድሜ ባይለግሰን ኖሮ ሰርተን በእጃችን በአደራ ያለውን ገንዘብና ንብረት ማግኘት ባልቻልን ነበር። የሰጠን እግዚአብሔር ነውና፣ የራሱን መልሰን ለመስጠት ውስጣችን አይጭነቀው።

### 1.3 እግዚአብሔርን መታዘዝ ለእግዚአብሔር መስዋእት ከማቅረብና ለእርሱ ከመስጠት ይበልጣል።

*"የእግዚአብሔርን ቃል በመታዘዝ ደስ የሚለውን ያህል፣ እግዚአብሔር ለሚቃጠል ቁርባንና መስዋዕት ደስ ይለዋልን? እነሆ መታዘዝ ከመስዋዕት፣ ማዳመጥም ከአውራ በግ ስብ ይበልጣል። (የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል)።" (1 ሳሙ 15፡22-23 - አ.መ.ት.)*

*እግዚአብሔር ከአገልግሎታችንና ለእርሱ ከምንሰጠው ነገር ሁሉ በላይና በፊት እርሱንና ቃሉን መታዘዛችንና በቃሉ መሰረት መኖራችን እጅግ ደስ ያሰኘዋል።*
*ለእነርሱም ለዘላለምም ለልጆቻቸው መልካም ይሆንላቸው ዘንድ፥ እንዲፈሩኝ ሁልጊዜም ትእዛዜን ሁሉ እንዲጠብቁ እንዲህ ያለ ልብ ምነው በሆነላቸው! (ዘዳ 5፡29)*
*እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ፥ የምድርን በረከት ትበላላችሁ። (ኢሳ 1፡19)*
*ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ። (ዮሐ 14፡15)*
*እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደ ጠበቅሁ በፍቅሩም እንደምኖር፥ ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ። (ዮሐ 15፡10)*

### 2. መስጠት በመጽሐፍ ቅዱስ

በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ መስጠት በብሉይና በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብዙ የተነሡ ዝርዝር ጉዳዮች አሉ። መስጠትን ካነሳን ሰፊ ሃሳብ አለው። ይሁን እንጂ በዚህ ትምህርታችን ውስጥ መሰረታዊ የሆኑ ሃሰቦችን ብቻ እናነሳለን። መስጠት የተለያዩ ይዘቶች /ዓይነቶች/ አሉት።

**የመስጠት ዓይነቶች**

**ሀ) እንደ ትእዛዝ የተቀመጠ ስጦታ**

- *አሥራት*

በዘፍጥረት ውስጥ ገና ስለ አስራት ዝርዝር የሆነ ትዕዛዝ ባልተሰጠበት ወቅት አብርሃም ግን የልዑል እግዚአብሔር ካህን ለነበረው ለንጉሱ ለመልከ ጼዴቅ አስራትን ሰጥቶታል።
*"አብራምም ከሁሉ አሥራትን ሰጠው" (ዘፍጥረት 14፡20)*


በመምህር ማዕረጌ ሐብቱ
+251 911 47 58 42

ከዚያ በኋላ ደግሞ ስለ አስራት ግልጽ የሆነ ትዕዛዝ በእግዚአብሔር ተሰጥቷል፡፡
*"የምድር አሥራት፣... የእግዚአብሔር ነው፤ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ነው፡፡" (ዘሌ 27፡30-33)*
*"ከእርሻህ በየአመቱ ከምታገኘው ከዘርህ ፍሬ ሁሉ አሥራት ታወጣለህ፡፡" (ዘዳ 14፡22-29)*
*". . . አሥራቱን ሁሉ ወደጎተራ አግቡ . . ." (ሚል 3፡10)*

- በኩራት

*"በእርሻም የምትዘራትን የፍሬህን በኵራት የመከር በዓል፥ ዓመቱም ሳያልቅ ፍሬህን ከእርሻ ባከማቸህ ጊዜ የመክተቻውን በዓል ጠብቅ፡፡"* (ዘፀ 23፡16)
*"የተመረጠውን የምድርህን ፍሬ በኩራት ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ቤት አምጣ፡፡" (ዘፀ 23፡19)*

**ለ) በበጎ ፈቃድ የሚደረግ ስጦታ (መባ)**
*"እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፡- ስጦታ ያመጡልኝ ዘንድ ለእስራኤል ልጆች ተናገር፤ በገዛ እጁ ሊሰጠኝ በልቡ ከሚያምረው ሁሉ መባ ተቀበሉ፡፡"(ዘፀ 25፡1-2)*
*"እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ፣ በሀዘን ወይም በግድ አይደለም፡፡" (2 ቆሮ 9፡6-7)*

3. **የመስጠት መርሆዎች**

**3.1 ክብርን በመፈለግ የሰውን ቀልብ ለመሳብ መሆን የለበትም [ግብዝነት የሌለበት ፡፡**
". . . በምትሰጡበት ጊዜ ይታይልኝ ብላችሁ አታድርጉ. . ." (ማቴ 6፡2)

**3.2 በየጊዜውና በቋሚነት መሆን አለበት**
*"ገንዘብ ማሰባሰብ የሚደረገው እኔ በምመጣበት ጊዜ እንዳይሆን ... በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን እየለየ ያስቀምጥ፡፡" (1 ቆሮ 16፡2)*

**3.3 በእውቀት መሆን አለበት**
ስንሰጥ ገብቶንና አውቀን መሆን አለበት፡፡ የምናውቀው ደግሞ፦ ኢየሱስ ያደረገውን ነው፡፡ እርሱ ሃብታም ሆኖ ሳለ እኛ ባለጠጎች እንሆን ዘንድ ስለ እኛ ድሃ ሆነ!
*"የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ጸጋ ታውቃላችሁና፤በእርሱ ድህነት እናንተ ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ እርሱ ሃብታም ሆኖ ሳለ ለእናንተ ሲል ድሃ ሆነ፡፡" (2 ቆሮ 8፡9)*

ፀጋን እንደሚሰጠንና የሚያስፈልገንን እንደሚያዘጋጅ ማወቅ አለብን፡፡
*"ሁልጊዜ በሁሉ ነገር የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ አግኝታችሁ ለበጎ ስራ ሁሉ እንድትተርፉ፣ እግዚአብሔር ጸጋን ሁሉ ሊያበዛላችሁ ይችላል፡፡" (2 ቆሮ 9፡8)*

**3.4 በፈቃደኝነት መሆን አለበት**
*"ለመስጠት በጎ ፈቃድ ካለን ስጦታው ተቀባይነት የሚያገኘው ባለን መጠን ስንሰጥ እንጂ፣ በሌለን መጠን ለመስጠት ስንሞክር አይደለም፡፡" (2 ቆሮ 8፡12)*

**3.5 በደስታ መሆን አለበት**
*". . . እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ሰው ይወዳል፡፡" (2 ቆሮ 9፡7)*


በመምህር ማዕረጌ ሐብቱ
+251 911 47 58 42

### 3.6 <u>እንደገቢው መጠን መሆን አለበት (እንደቀናው)</u>

*"ለመስጠት በጎ ፈቃድ ካለን ስጦታው ተቀባይነት የሚያገኘው <u>ባለን መጠን</u> ስንሰጥ እንጂ፣ በሌለን መጠን ለመስጠት ስንሞክር አይደለም::" (2 ቆሮ 8:12)*

*"ገንዘብ ማሰባሰብ የሚደረገው እኔ በምመጣበት ጊዜ እንዳይሆን፣ ከእናንተ እያንዳንዱ <u>እንደ ገቢው መጠን</u> በሳምንቱ መጀመርያ ቀን እየለየ ያስቀምጥ::" (1 ቆሮ 16:2)*

### 3.7 <u>በበረከት መስጠት (በልግስና መስጠት) ይኖርብናል ::</u>

*"የደረሰባቸው መከራ ጽኑ ቢሆንም ደስታቸው ግን የላቀ ነበር፤ ድህነታቸው ብርቱ ቢሆንም ልግስናቸው ግን የበዛ ነበር::" (2 ቆሮ 8:2)*

## 4. <u>ለምን እንሰጣለን ?</u>

### 4.1 <u>የተቸገሩትን ለመርዳት (ለመደገፍ) - በዚህም ፍቅራችንን ለማግለፅ ::</u>

*መቄዶንያና አካይያ በኢየሩሳሌም ካሉት ቅዱሳን መካከል የሚገኙትን <u>ድሆች</u> ለመርዳት ተነሳስተዋል:: (ሮሜ 15:26)*

*ይህ የምትሰጡት አገልግሎት የቅዱሳንን <u>ጉድለት</u> የሚያሟላ. . . ነው:: (ቆሮ 9:12-15)*

### 4.2 <u>የቤተክርስቲያንን አገልጋዮችን ለመደገፍ::</u>

*የፊልጵስዩስ ሰዎች ሆይ፥ ወንጌል በመጀመሪያ ሲሰበክ፥ ከመቄዶንያ በወጣሁ ጊዜ፥ ከእናንተ ብቻ በቀር ሌላ ቤተ ክርስቲያን በመስጠትና በመቀበል ስሌት ከእኔ ጋር እንዳልተካፈለች እናንተ ደግሞ ታውቃላችሁ፤ በተሰሎንቄ እንኳ ሳለሁ፥ አንድ ጊዜና ሁለት ጊዜ ያስፈለገኝን ሰዳችሁልኝ ነበርና:: (ፊል 4:15-16) "በችግሬ ወቅት ደግማችሁ እርዳታ ልካችሁልኛልና::" (ቁ.16 አ.መ.ት.) "የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋል::" (1 ጢሞ 5:17-18፤ዘዳ 25:4)*

### 4.3 <u>ወንጌልን ለማሰራጨትና ሰዎችን ደቀ መዛሙርት ለማድረግ</u>

ሰዎችን በመንጌል ለመድረስና እነዚህን በክርስቶስ ፍቅር ተነክተው ወደ እርሱ የመጡትን ሰዎች ደቀ መዛሙርት በማድረግ ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ራሳቸውን የሰጡ ሰዎች እንደሚያስፈልጉ ሁሉ ይህንን አገልግሎት ለመፈጸም ገንዘብም ያስፈልጋል::

### 4.4 <u>መስጠት የቤ/ክንን አንድነት የማምጣትና የመጠበቅ ውጤት ስላለው ::</u>

*"መቄዶንያና አካይያ በኢየሩሳሌም ቅዱሳን መካከል ያሉትን ድሆች ይረዱ ዘንድ ወደዋልና:: እርዳታ ለማድረግ ወደዋል፤ በእርግጥም ባለ ዕዳዎች ናቸው:: አሕዛብ የአይሁድ መንፈሳዊ በረከት ተካፋዮች ከሆኑ፣ ያገኙትን መንፈሳዊ በረከት ከአይሁድ ጋር ይካፈሉ ዘንድ የእነርሱ ባለ ዕዳዎች ናቸው::" (ሮሜ 15:26-27)*

## 5. <u>የመስጠት ውጤቶች</u>

1) እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛል (2 ቆሮ 9:7፤ 2 ቆሮ 5:9)
2) መስጠት ፅድቅ እንዲገለጥ ያደርጋል (2 ቆሮ 9:10)
3) የተቸገሩት እንዲረዱና ጉድለታቸው እንዲሞላ ያደርጋል (2 ቆሮ 9:12)
4) ምስጋና ለእግዚአብሔር እንዲበዛ ያደርጋል (2 ቆሮ 9:12)
5) ፀሎትን ያነሳሳል ፣ ያበረታታል (2 ቆሮ 9:13-14 )
6) የእግዚአብሔርን ፀጋ ያጎላል ፣ ይገልጣል (2 ቆሮ 9:14)
7) እግዚአብሔር ይከበራል (2 ቆሮ 9:13)



በመምህር ማዕረጌ ሐብቱ
+251 911 47 58 42

### 6. <u>የእግዚአብሔር ፀጋ በመስጠት ውስጥ</u> (2 ቆሮ 8፡1-13)

*ወንድሞች ሆይ፥ ለመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ጸጋ እናስታውቃችኋለን፤(2 ቆሮንቶስ 8፡1)*

የእግዚአብሔር ፀጋ በየትኛውም የሕይወት አቅጣጫ እንደሚያስፈልገን ሁሉ በመስጠትም የእግዚአብሔር ፀጋ ያስፈልገናል። በዚህ አቅጣጫ እግዚአብሔር ለመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት የሰጠውን የእግዚአብሔር ፀጋ በመመልከት የእኛም ሕይወት በዚህ አቅጣጫ እንዲለወጥ ልባችንን መክፈቱ አስፈላጊ ይሆናል። ለመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት አማኞች ይህ ፀጋ ያመጣው ለውጥ ምንድን ነው? ከመስጠት አቅጣጫ የእግዚአብሔር ፀጋ በሕዝቡ ላይ የሚያመጣው ታላቅ ለውጥ በእርግጠኝነት አለ!

#### 6.1 <u>የእግዚአብሔር ፀጋ የመስጠትን ሕይወት እንድንለማመድ ያደርገናል</u> ።

*"ለመቄዶንያ አብያተክርስቲያናት የተሰጠውን የእግዚአብሔር ፀጋ እናስታውቃችኋለን።" (2 ቆሮ 8፡1)*

ጳውሎስ በዚህ ክፍል የሚናገረው ስለ <u>ፀጋ</u> ቢሆንም እንኳ መሠረታዊ ሃሳቡ ግን <u>ገንዘብ መስጠትን</u> የሚመለከት ነው። በዚህ አቅጣጫ በመቄዶንያ አብያተክርስቲያናት የተገለፀውን ፀጋ እንድናውቅ ለእኛም ይፈልግብናል።

#### 6.2 <u>የእግዚአብሔር ፀጋ በደስታ እንድንሰጥ ያደርጋል</u> ።

*"በብዙ መከራ ተፈትነው ሳሉ የደስታቸው ብዛትና . . ." (2 ቆሮ 8፡2ሀ)*

በብዙ መከራም ቢያልፉም ደስ እያላቸው (በደስታ) ይሰጡ ነበር።

#### 6.3 <u>የእግዚአብሔር ፀጋ በልግስና እንድንሰጥ ያደርጋል</u> ።

*"የድህነታቸው ጥልቅነት የልግስናቸውን ባለጠግነት አብዝቶአል።" (2 ቆሮ 8፡2ለ)*

ምንም እንኳ ጥልቅ ድህነት ቢኖርባቸውም ለመስጠት ግን እንዳይችሉ አላደረጋቸውም። ይልቁንም ልግስናቸውን አበዛው።

#### 6.4 <u>የእግዚአብሔር ፀጋ ከጉድለታችን (ከአቅማችንም በላይ) እንድንሰጥ ያደርጋል።</u>

*"ከአቅማቸው የሚያልፍ እንኳ ወደው እንደሰጡ እመሰክርላቸዋለሁና።" (2 ቆሮ 8፡3)*

ፀጋው እንደ አቅማቸው ደግሞም በዙሪያቸው ካለው ሁኔታ (ከድህነታቸው) በላይ፣ ከአቅማቸው በላይ ወድደው እንዲሰጡ አድርጎአቸዋል። ብዙዎቻችን እንደአቅማችን እንሰጥ ይሆናል። አንዳንዶቻችን እንዲያውም እንደ አቅማችንም ቢሆንም አንሰጥም ይሆናል። ግን ስንቶቻችን ነን ከአቅማችን በላይ የምንሰጠው?

ይህ መስዋዕትነት የሚጠይቅ መስጠት ነው። *ይህንን እንዲያደርጉ የረዳቸው ደግሞ የእዚአብሔር ፀጋ ነው።*

#### 6.5 <u>የእግዚአብሔር ፀጋ በፈቃደኝነት እንድንሰጥ ያደርጋል</u> ።

*"ለቅዱሳን በሆነው አገልግሎት እንዲተባበሩ ይህን ቸርነት <u>በብዙ</u> <u>ልመና</u> ከእኛ ይለምኑ ነበር።" (2 ቆሮ 8፡7)*


በመምህር ማዕረጌ ሐብቱ
+251 911 47 58 42

### 6.6 <u>የእግዚአብሔር ፀጋ ስጦታችን ራሳችንን ለጌታ መስጠታችንን የምንመሰክርበት ያደርገናል</u>።

*"አስቀድመው በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን ለጌታ ለእኛም ሰጡ ...።" (2 ቆሮ 8፡5)*
ገንዘባቸውን ከመስጠታቸው በፊት ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ለጌታ ሰጥተዋል። ራሳቸውን ከሰጡ ደግሞ ገንዘባቸውንና ያላቸውን መስጠት አይቸገሩም።

### 6.7 <u>የእግዚአብሔር ፀጋ ሰዎች በብዙ ነገሮች እንደሚያውቁን ሁሉ በመስጠትም (በቸር ሥራ) ለሌሎች እንድንተርፍ ያደርገናል። በመስጠትም እግዚአብሔር ፀጋ ይለካል።</u>

*". . . በዚህ ቸር ስራ ደግሞ ትረፉ።" (2 ቆሮ 8፡7)*
የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በእምነት፣ በቃል፣ በእውቀት፣ በትጋት፣ በፍቅርም ይታወቁ ነበር። አሁን የሚቀራቸው ደግሞ በመስጠት (በቸር ሥራ) ለሌሎች መትረፍ ነው።
የእግዚአብሔር ፀጋ በሕወታችን ሲሰራ የምንለካው ወይም የምንመዝነው በዚሕ መንገድ ነው ። መስጠትን መለማመድ አለብን። ይህ ደግሞ አንደ ማንኛውም የሕይወት አቅጣጫ ፀጋ የሚጠይቅ ነው። መስጠት በእግዚአብሔር ፀጋ እውን ይሆናል!

### 6.8 <u>የእግዚአብሔር ፀጋ በመስጠት ለሌሎች ያለንን ፍቅር እንድናረጋግጥ የደርጋል።</u>

*"ትእዛዝ እንደምሰጥ አልልም፣ ነገር ግን በሌሎች ትጋት በኩል የፍቅራችሁን እውነተኛነት ደግሞ ልመረምር እላለሁ።" (2 ቆሮ 8፡8)*
በዚህ ክፍል ውስጥ "<u>ትዕዛዝ እንደምሰጥ አልልም</u>" ይላል። ነገር ግን "<u>መስጠት ትእዛዝ አይደለምና ላልሰጥም እችላለሁ" ማለት ትችላለህን?</u> በእርግጥ ይህ በበጎ ፈቃድ የሚደረግ ስጦታ እንጂ በግዴታ የሚደረግ ትእዛዝ አይደለም። ነገር ግን የቁጥር 8 ቀጣይ ሃሳብ ስንመለከት እንዲህ በማለት ይናገራል፦ "ነገር ግን በሌሎች ትጋት በኩል <u>የፍቅራችሁ እውነተኛነት</u> ደግሞ ልመረምር እላለሁ። "በአጭሩ ጳውሎስ የሚለው "ፍቅር ካለህ በመስጠት አረጋግጥ" ነው። እንግዲያውስ መስጠት ፍቅራችን የሚረጋገጥበት ቁልፍ ነገር ነው። "ስለ መቄዶንያ ክርስቲያኖች ፍቅር ምንም ዓይነት ጥያቄ የለኝም። ፍቅራቸውን በመስጠት አረጋግጠዋል።" በማለት ጳውሎስ ይመስክራል።

### 6.9 <u>የእግዚአብሔር ፀጋ በመስጠት ክርስቶስን የሚመስል ሕይወት እንድንኖር ይረዳናል።</u>

*"የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቸር ስጦታ አውቃችኋልና፤ እናንተ በእርሱ ድህነት ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ድሀ ሆነ።" (2 ቆሮ 8፡9)*
ኢየሱስ ባለጠጋ (ሃብታም) ሆኖ ሳለ ስለ እኛ ድሀ በመሆን ምሳሌ ሆነልን።

### 6፡10 <u>የእግዚአብሔር ፀጋ ስጦታችን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለውና የተወደደ እንዲሆን ያደርጋል ።</u>

*". . . የተወደደ ይሆናል . . . " (2 ቆሮ 8፡11-12)*
ለእግዚአብሔር እንዳለን መጠን ስንሰጥ ስጦታችን በእርሱ ፊት ተቀባይነት ያለውና የተወደደ ይሆናል። እርሱም ደስ ይሰኛል።
*ይህ ማለት ካለን በላይ አንሰጥም ለማለት ሳይሆን <u>ከሌላው ጋር እየተፎካከርን</u> <u>አንሰጥም ለማለት ነው ።</u>


*በመምህር ማዕረጌ ሐብቱ*
+251 911 47 58 42

### 6.10 <u>የእግዚአብሔር ፀጋ በስጦታችን ምክንያት በቅዱሳን መካከል አንድነትንና እኩልነትን በመፍጠር ቤተክርስቲያን እንድታድግ ያደርጋል</u> ፡፡

*"ለሌሎች እረፍት ለእናንተም መከራ እንዲሆን አይደለም፣ <u>ትክክል</u> <u>እንዲሆን</u> ነው እንጂ፤" (2 ቆሮ 8፡13-15) ". . . <u>ሁላችሁ እኩል እንድትሆኑ ነው</u>፡፡" (ቁ. 13 አ.መ.ት.)*

## 7. <u>የመስጠት በረከቶች</u>

### 7.1 <u>በመስጠት በሰማይ መዝገብ ማከማቸት አለ</u>፡፡

ማቴ 6፡1-4, 19-24

ኢየሱስ ስለ መስጠት ካስተማረ በኋላ *"ነገር ግን ብል ሊበላው ፣ዝገት ሊያበላሸው፣ ሌባም ቆፍሮ ሊሰርቀው በማይችልበት በዚያ በሰማይ ለራሳችሁ ሀብት አከማቹ፤"* (ማቴ 6:20) በማለት ተናገረ፡፡

በዚህ ዓለም ላይ ለእግዚአብሔር ብለን የምናደርገው ማንኛውም መልካም ስራ በሰማይ እንደተከማቸ ሃብት ይቆጠርልናል ፡፡

### 7.2 <u>በንፁህ ልብና ህሊና ለእግዚአብሔር የሚሰጡ አማኞች ምድራዊ በረከትም ተስፋ ተገብቶላቸዋል</u>፡፡

*"በቤቴ ውስጥ መብል እንዲሆን አስራቱን ሁሉ ወደጎተራ አግቡ፤ የሰማይንም መስኮት ባልከፍትላችሁ፣ በረከትንም አትረፍርፌ ባላፈስላችሁ በዚህ ፈትኑኝ፡፡" (ሚል 3፡10)*

*"ስጡ ይሰጣችሁማል፡፡" (ሉቃ 6፡38)*

*"እግዚአብሔርን ከሃብትህ አክብር፣… ጎተራህም እህልን ይሞላል …፡፡" (ምሳሌ 3፡9-10)*

ይህንን ስንል ለእግዚአብሔር የሚሰጥ ሁሉ ሚሊየነር ይሆናል፣ የግድ በሰው መለኪያ እጅግ ባለጠጋ ይሆናል ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን ለእግዚአብሔር የሚሰጠ በራሱ በእግዚአብሔር መለኪያ ከሰጡት በላይ በተለያየ አቅጣጫ ይባርካቸዋል ማለት ነው ፡፡ ይህም ደግሞ መንፈሳዊውንም ሥጋዊውንም (በዚህ ምድርም) ይጨምራል ፡፡

### 7.3 <u>መስጠትን ስንለማመድ ከስስት ሕይወት እንድንወጣና እንድንላቀቅ ያደርገናል</u> ፡፡

*"ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነው…" (1 ጢሞ 6፡10)*

### 7.4 <u>መስጠት እምነታችን በተግባር እንዲገለጥ (እምነታችን በተግባር/በሥራ እንዲገለጥ) ያደርገጋል</u>፡፡

*"ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው፡፡" (ያዕ 2፡15-17)*

መፅሐፍ ቅዱስ "**<u>መታዘዝን</u>**" መሠረት በማድረግ ብዙ <u>የበረከት ተስፋ ቃሎች ሰጥቷል</u>፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ለምን እንደሚባርከን ዝርዝር መግለጫ ይኖረናል ማለት አይደለም፣ አናውቀውምም፡፡ አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር በረከቱን ሊይዝብን ይችላል ይሁን እንጅ ምክንያቱን በግልፅ ላናውቀው እንችላለን ፡፡

ገንዘቡን ለእግዚአብሔር የሚሰጥ ሰው የገንዘብ ችግር አይኖርበትም ማለት አይደለም፡፡ የገንዘቡ ችግር በሃጢዓት ምክንያት ነው ብንል ደግሞ እንደ ኢዮብ አፅናኞች ስህተት ውስጥ እንገባለን ፡፡ አሠራሩ የእግዚአብሔር ነው፡፡

ፊል 4 ፡ 12
ኢዮብ 1 ፡ 21


በመምህር ማዕረጌ ሐብቱ
+251 911 47 58 42

*"በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ያጭዳል፣ በበረከትም የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል።"* (*2 ቆሮ 9፡ 6)* የሚለው ቃል ግራ የሚያጋባ ሳይሆን ግልፅና ግልፅ ነው። እንደሚነበበው ነው። ነገር ግን አስራቱን፣ በኩራቱንና መባን የሚሰጥ ሰው የገንዘብ ችግር አይገጥመውም ማለት ነው ወይ? በፍፁም አይደለም! ለምን? አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር እኛን ለመፈተን ፊቱን ሊሰውርብን ይችላል።

2 ዜና 32፡31

ኢዮብ 1:9

ስለዚህ ስንሰጥ የምንሰጠውን ሳይሆን ልባችንን (motive) መመዘን አለብን። ስለዚህ በረከት እንዲጨመርልን በማሰብ በትርፍ ስሌት የምንሰጥ ከሆነ ተሳስተናል፣ እግዚአብሔርም ሥጦታችንን አይወደውም። እንደ አማኞች ገንዘባችንን ስንሰጥ "ባይሆንም እንኳ" በሚል እምነት ቆመን መሆን አለበት። ይህ እውነት ደግሞ በሲድራቅ ሚሳቅና አብደናጎ የተረጋገጠ ነው። እነርሱ እንደዚህ አሉ፦ "ናቡከደነፆር ሆይ ፥በዚህ ነገር እንመልስልህ ዘንድ አስፈላጊያችን አይደለም። የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል፤ ከእጅህም ያድነናል፥ ንጉስ ሆይ! ነገር ግን፥ ንጉስ ሆይ፥ እርሱ ባያድነን፥ አማልክትህን እንዳናመልክ ላቆምኸውም የወርቁ ምስል እንዳንሰግድለት እወቅ አሉት።" (ዳን 3፡16-18)



በመምህር ማዕረጌ ሐብቱ
+251 911 47 58 42